# የአምባሳደሩ ጉብኝት

አንድ የውጭ ሃገር አምባሳደር ተሹመው ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጡ አዲስ አበባን ለመጎብኘት መኪናቸውን ይዘው ከአራት ኪሎው ቤተ መንግስት ይነሳሉ። ከዚያም 4ኪሎ ሃውልቱን አለፍ እንዳሉ ተማሪዎች ያዩና አንዱን ጠርተው ይሄ መንገድ ወደ አሜሪካ ኤንባሲ ይወስደኛል ብለው ይጠይቁታል። ተማሪውም Yes ብሎ ይመልስላቸውና ጉዞ ይቀጥላሉ። አሁንም 6ኪሎ ሃውልት አካባቢ ሲደርሱ ሌሎች ተማሪዎች ያዩና አንዱን ጠርተው ይጠይቁታል።ተማሪውም yap በማለት ይመልስላቸውና ይቀጥላሉ።

በመቀጠልም አሜሪካ ኤንባሲ አካባቢ ሲደርሱ አሁንም ሌሎች ተማሪዎች ያዩና አንዱን ጠርተው ይህ ነው የአሜሪካ ኤንባሲ ብለው ይጠይቁታል። እሱም አዎ ብሎ ይመልስላቸዋል። አምባሳደሩም የሰሙት የተለያየ መልስ እየገረማቸው ነበርና በሌላ ጊዜ ለአንዱ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን አንድ ጥያቄ ለ3 የተለያዩ ተማሪዎች አቅርበው የተለያዩ ምላሾች እንዳገኙ በመግለጽ መገረማቸውን ይነግሩታል።

ባለስልጣኑም በነገሩ ምንም የተደነቀ ሳይመስል በመኩራራት እንዲህ ያስረዳቸዋል። Yes ብሎ 4ኪሎ ላይ የመለሰልዎት የምኒሊክ 2ኛ ደረጃ ተማሪ ነው። 6ኪሎ ላይ yap በማለት የመለሰው ደግሞ የ6ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው።አሜሪካ ኤንባሲ አካባቢ አዎ ያልዎት የአምሃ ደስታ 1ኛ ደረጃ ተማሪ ነው። ብሎ ሲያስረዳቸው። በፈጣን መልሱና በትንታኔው ተገርመው እርግጠኛ ነህ ? ብለው ይጠይቁታል።

እሱም አዎ ብሎ ይመልሳል። አንተም የአምሃ ደስታ _ _ _ _ ነህ ነው ነገሩ።